# ህያው ሰማዕታት

ጥቅምት 2003
abraham beyenne

የጦር አግማሱ በለስ ሲነሳው
ሸጉጡን ጠጥቶ እንደ መይሳው
በጠላቱ ላይ የተቀናጣ
ካፊሙዙ ጫፍ ጥም የተወጣ
ጥላሁን ማኦ ከንዱ ሳይላላ
በጀግና ደሙ የቀላ
ሻውልት አኑሯል በገላ ።

ሌላው ስማእት አንበሳ
ከደንቢያ እስከ በለሳ
በዝናው እጅ እያስነሳ
ቡከን አርጎ የቁም እሬሳ
ባንዳውን ሁሉ እያሸበረ
እንቅልፍ ነስቶ የኖረ
ጥቁሩ ሌኒን ገናናው
ሸጉጡን ጠቶ ጀግናው
ከዱን ሲንትራስ ጆቢራ
አንገቱን ቆርጦው በገጀራ
ተንሰዩ ማርያም ወገራ
የእጅ መንሻ ያደረጉት
እንደ ገጀራው ዝገት
ወንጀላቸውን አፈር በልቶት
ሳይወራረድ ሂሳቡ
ፋይሉ እንዳይዘጋ መዝገቡ
አደራ ሲኳት እማማ
የሚለባለብ ሳማ
እሾህ ጋሬጣ አቃቅማ
የሚኮሰኩስ አባ ጨጓሬ
የሚከነክን በርበሬ
ማብቀል ተስኗት አገሬ
የማሌሊት ዝላይ ማዘንበያ ማቶት
ግኡዝ ሆነ ሀዝቧ ስብእናው ከድቶት።

ጥቅምት 2003
abraham beyenne